# ጋዜጠኛ ወይስ ጋሬጠኛ

ጋዜጠኛ፣ምን ማለት ነው? ወሬ ነጋሪ ወይስ አሽባሪ፣ጸሃፌትዕዛዝ፣አፈ መንግሥት ወይስ አፈ-ንጉሥ፣አሉቧልተኛ ወይስ ነገረኛ፣ አወዳሽ ወይስ አጋላጭ፣ እበላባይ ወይስ አድርባይ፣ዘጋቢ ወይስ ዘካሪ፣ መጋቢ ወይስ ተመጋቢ፣አሳሳች ወይስ መካሪና አስተማሪ፣ ሙያተኛ ወይስ ቅጥረኛ?እስኪ በነዚህ ጸባያትና ተግባራት ጋጤጠኛን እንፈትሸው።

በትክክለኛው ትርጓሜ ጋዜጠኛ ማለት በአጭሩ ወሬ ወይም ዜና አቅራቢ(አድራሽ)ማለት ነው።የወሬው ይዘት የተለያዩ እርእሶችን የሚመለከት ይሆናል።ጋዜጠኝነት ወይም (journalism) አስፈላጊነቱ ታውቆለት የተጀመረው በከበርቴ አገራት ሲሆን በዓለም አቀፍ ደረጃ እየተስፋፋ የመጣ የሙያ ዘርፍ ነው። እያንዳንዱ የማህበረሰብ እንቅስቃሴ ማለትም በፖለቲካው፣በኤኮኖሚው፣በማህበረሰብ ጉዳይና እንቅስቃሴ፣በእስፖርትና ባሕል ዙሪያ፣ በፍትሕ ዙሪያ፣በቤተሰብ ጉዳይ፣በልጆች አስተዳደግ፣በከባቢ የተፈጥሮ ክስተቶች፣ ገጽታና የአዬር ለውጥ መረጃ(ሜትሮሎጂ)፣የጦርነት፣የሳይንስና ምርምር ውጤቶችን፣ በመንፈሳዊ (ሃይማኖታዊ) መልእክቶችና ክንውኖች፣አገራዊና ዓለም አቀፋዊ ጉዳዮችን፣ክስተቶችን ተከታትለው በዝርዝርና በማስረጃ ለማህበረሰቡ የሚያቀርቡበት በቂ እውቀትና ስልጠና የሚወስዱበት ሙያ ነው። በአሠራሩም አንዱ ጋዜጠኛ ከሰለጠነበት ውጭ በማያውቀውና በማይረዳው መስክ፣በሌላው የሥራ ዘርፍ ውስጥ ገብቶ አይዘባርቅም፤አይፈተፍትም። ሙያው የራሱ የሆነ መስፈርትና መመዘኛዎች፣ ስነምግባርና ተአማኒነት(ethics and Integrity) አለው።ስለሆነም ከአንዱ ጠርዝ ወደሌላው ጠርዝ ተስፈንጥሮ ያሻውን የሚዘላብድበት ሜዳ አይደለም። ዘጋቢ ብቻ ሳይሆን መርማሪና ተመራማሪም፣አድራሽ ብቻም ሳይሆን ፈታሽ ጭምር ነው።ለሚያቀርበው ዜና ወይም ትችት በቂ ችሎታና ዕውቀት ሊኖረው ይገባል። ጋዜጠኛ ወገንተኛ ሆኖ ከአንዱ ጋር ብቻ ልጥፍ አይልም። የአንድ ፖለቲካ ድርጅት ልሳንም አይሆንም። በአገራዊ ቁመና ላይ ሆኖ ሁሉንም በእኩል ዓይን እያዬ ሚዛናዊ አስተያዬት ይሰጣል።አንዱን አስደስቶ ሌላውን ለመውቀስና ለማጋለጥ አይሰማራም።በበላበት የሚጮህ ውሻ አይደለም።ጋዜጠኛ መልእክቱን በጽሑፍ ወይም በድምጽ ያስተላልፋል።ሁሉም ጋዜጠኛ የመጻፍ ችሎታ መኖር ሲገባው የሚጽፍ ሁሉ ግን ጋዜጠኛ ነው ማለት አይደለም። ማይክሮፎንም ጨብጦ የሚያወራ ሁሉ ጋዜጠኛ ነው ማለት አይደለም።በአነባበብ ስልትና የድምጽ ጥራት ተመርጠው የሚመደቡ ሊኖሩ ይችላሉ።ጋዜጠኛ ልዩ ልዩ ቋንቋዎችን የመቻሉም ብቃት አንዱ ወሳኝ ነው። በዓለም አቀፉ ማህበረሰብ ውስጥ የሚከሰቱትን ለማወቅና ለማድረስም ያስችለዋል።

የጋዜጠኝነት ሙያ የተሰለፉ ሰዎች ወይም ተቋማት በህብረተሰቡ ውስጥ የሚንጸባረቁ ሁለገብ ክስተቶችንና ሁኔታዎችን፣ እዬተከታተሉ የሚጠቅመው እንዲ ጎለብት፣የሚጎዳው እንዲታረም ወይም እንዲወገድ የሚጠቁሙ፣ የሚመክሩና የሚያስተምሩ ናቸው። የመንግሥትና መሪዎችንም ተግባር እዬተከታተሉ ለሕዝቡ በማቅረብ ከጥፋት እንዲታረሙ

ይመክራሉ። ቀውስና አደጋ ሲደርስ በቦታው ላይ ቀድመው በመድረስ የአደጋውን መነሾ፣ ያደረሰውን ጉዳት በዝርዝር በማቅረብ ሌላው ከተመሳሳይ አደጋ እንዲድን ያሳስባሉ፤ ትምህርት ይሰጣሉ።ጥፋት ሲፈጸም በማስረጃ ተንትነው ካለምንም ፍርሃትና ይሉኝታ የሚያጋልጡ፣አጥፊው ለፈጸመው ጥፋት ተገቢውን ቅጣት እንዲያገኝ የሚያሳስቡ አይንና ጆሮ፣የማህበረሰቡ ጠባቂ ዘቦች ወይም በእንግሊዝኛው (Watch Dogs)ለድምጽ አልባውም ልሳን ተብለው ህብረተሰቡን የሚያገለግሉ ፣ለሙያቸው ያደሩ ናቸው።

ጋዜጣ በአጭሩ ሲተረጎም በጽሁፍ የዜና ማብሰሪያ ወረቀት ማለት ነው።ጋዜጠኛ ማለትም ያንን የጽሁፍ ዜና የሚያዘጋጅ ማለት ነው።ከጊዜ ብዛት የጋዜጠኛ የዜና አቀራረብ በመልክም በይዘትም ተለውጧል።በስልክ፣በራዲዮ በቴፕ ሪኮርደር፣ምስልንና ድምጽንም በማቀላቀል በቪድዮና በቴሌቪዥን በስዕል በካርቶንና በግራፊቲ፣የተቀረጹ መልእክቶችን በቀጥታና በተዘዋዋሪ የማሳለፉ ዘዴ ተለምዷል።ቀደም ካለው የቴሌግራምና የስልክ ዘገባም የኮድ ልውውጥ የጋዘጠኞች መጠቀሚያ መሆኑ ተሻሻለ እንጂ አልተቀዬረም።የኢንተርኔት መፈልሰፍ የዜና ፍጥነትና መጠኑን አብዝቶታል።አንድ ጋዜጠኛ ከቦታ ቦታ የመኼዱን ግዴታ ቀንሶለታል።በሳተላይት መረጃ እቤቱ ቁጭ ብሎ ቅጽበታዊ ዘገባውን ይሠራል። በወረቀት፣በጋዜጣ ላይ (journal) ይቀርብ የነበረው ዜና አሁን ላይ እዬቀነሰ መጥቷል፣ የቀረው ጋዜጠኛ የሚለው ስያሜ ብቻ ነው።ሆኖም ግን እሱም ቢሆን ዜና አቅራቢና ዜና አንባቢ በሚለው ተቀይሯል።

በአገራችን ጋዜጠኛ ተብሎ በተዘረጋው የሙያ ዘርፍና በሌሎቹ የሲነ-ኪነት(የችሎታ) ስጦታዎች ያሉትን አሠራሮች በሰለጠኑት ብሎም ለሙያ ዘርፉ መፈጠር ምክንያት ብሎም አስፈላጊነት ትኩረት ሰጥተው ከሚጠቀሙበት አገራት ጋር ስንመዝነው ከላይ በተዘረዘሩት ብዥታዎች ውስጥ ይከቱናል።ስምና ግብራቸው አልጣጣም ይላል።

በቀድሞ ጊዜ በአገር ውስጥ የሚከሰቱትን ድርጊቶች በተለይም የመሪዎቹን የመንግሥታቱን(የነግሥታቱን )ገድልና ውሎ(ዜና መዋዕል) በመሆን፣ለሕዝቡ በማሳወቅ ሕዝብ ለመሪዎቹ ክብርና ፍቅር እንዲኖረው ፣አገዛዙና ግንኙነቱ ፍጹም ሰላማዊና ተቃውሞ የሌለው ለማድረግ የሚሰብኩ የቤተመንግሥቱ አፈ ቀላጤዎች ወይም ቃል አቀባዮች እንደነበሩ ታሪክ ይነግረናል።የመሪዎችን ስብእና በማጉላት፣ ከፈጣሪ ጋር ግንኙነት እንዳላቸውና በፈጣሪ የተመረጡ እንደሆነ አድርገው በማቅረብ የሚፈሩና የሚከበሩ እንዲሆኑ በነዚህ አወዳሽ ግለሰቦች ምክንያት የመንግሥታቱ አገዛዝ ሳይረበሽ እንዲኖር ረድተዋል።ለዚህ አገልግሎታቸው የሃብትና የሹመት ዳረጎት ያገኙ ነበር ፣ የማእረግ ስምም አፈ ንጉሥ (ስለንጉሡ የሚናገር-፣ጸሐፊ ትእዛዝ ስለንጉሡ የሚጽፍ)ዜና መዋዕልና ዝክረ ነገሥት ስለነገሥታቱ ውሎና ሥራ የሚተርክና በጽሁፍ የሚመዘግብ ተብለው ይመደባሉ።ከሕዝቡ መሃል ሆነው ስለሕዝቡ የሚጽፉና የሚተርኩ አልነበሩም። ለመጻፍ ዕድሉና ችሎታ የነበራቸው የቤተክህነት ሰዎች በመሆናቸው ፍትሓ ነገሥትና ክብረነገሥትን ከእምተቱ ጋር በማያያዝ የሚጽፉ እንጂ ስለሕዝባዊ ፍትሕ የጻፉ

አልነበሩም።ለሰማያዊው እንጂ ለመሬቱ ኑሮ መስተካከል ግድም አይላቸውም ነበር፤ የሕዝቡ ልሳን በመሆን አላገለገሉም።ሌሎቹ ደግሞ የአገዛዙን መልካም ገጽ በማጉላት በዘፈንና በቲያትር የሚያሞግሱት የስነ-ኪነት ባለሚሎች ናቸው።

ንጉሡ ጠላት ሲነሳበትና ለመዝመት ሲነሳ የከተት አዋጁን እዬዞሩና እዬተቀባበሉ፣መለከት እዬነፉና ነጋሪት እዬጎሸሙ ለሕዝቡ የዝመት ጥሪውን የሚያስተላልፉ የጦር አብሳሪዎች እንደነበሩ ታሪክ ይመሰክራል።እነዚህ ከላይ የተገለጹት ሁሉ የዘመኑ ወሬ ነጋሪ ወይም ጋዜጠኞች ነበሩ ማለት ነው።እዚህ ላይ መለዬት ያለብን እውነተኛ  የታሪክ ጸሃፊዎችና ሁኔታን እንደአመጣጡ ተከታትለው ለሕዝብ የሚያሳውቁ፣ትክክል ያልሆነውን የሚቃወሙና የሚያጋልጡ ደፋሮች እንደነበሩ ልብ ማለት ያስፈልጋል።ጥቂትና ካለመደራጀታቸው የተነሳ ድምጻቸው እንዳይሰማ ብዙ ጭነትና መከራ ይጣልባቸው እንደነበር መካድ አይገባም።ሞት ፣መታሰር፣መሰደድ እጣ ፈንታቸው ነበር።አሁንም ነው።

በጥንቱ ጊዜ የዘመናዊ ጋዜጠኞችን የአሠራር ስርዓትና ወግ የተከተለ ሳይሆን፣ ስላልተለመደም የነበሩት ወሬ ነጋሪ ወይም መዋለ ነገሥታቱን የሚያበስሩ፣የሚያወድሱ የአምላክ ምትክ በማድረግ የሚያቀርቡና የሚዘግቡ፣የንጉሡን ትዕዛዝ ለሕዝቡ የሚያስተላልፉ በመሆናቸው የሕዝቡን ብሶት፣የሚያንጸባርቁ የሕዝብ ልሳን፣የንጉሡን ወይም የመሪዎችን ግድፈት የሚተቹ ደፋር ዜጎች አልነበሩም፣አሁንም አይደሉም። እንጀራቸው ከንጉሡ ወይም ከመሪዎቹ  ውዳሴ ጋር የተያያዘ ስለሆነ ንጉሡን ባወደሱበት መጠን ለሚወረወርላቸው እንጂ ለእውነት ቆመው በመመስከር  በራሳቸው ላይ የሚደርስባቸውን ለመቀበል ወኔው አልነበራቸውም።ከህሊናቸው ይልቅ ለሆዳቸው ማደርን የመረጡ ነበሩ።ናቸውም።

ጋዜጠኝነት እንደ ሙያ ዘርፍ ተወስዶ ስልጠናና ትምህርት መስጠት ከጀመረበት ጊዜ ወዲህ ብዙ ጋዜጠኞች ተፈጥረዋል።በአገርና በውጭ አገራት በከፍተኛ ደረጃ የተመረቁ ጋዜጠኞችም ቁጥራቸው ቀላል አይደለም።ሆኖም ግን በተማሩበት መስከ መርሃ ግብር ኤቲክስና ህግ መሰረት አደራቸውን የተወጡት በጣም ጥቂቶች ከመሆናቸው የተነሳ የሉም ማለቱ ይቀላል።ሙያው አንዱ የመንግሥት ተቋም ሆኖ በመወሰዱ ጋዜጠኞቹ የመንግሥት ቅጥረኞች ከመሆናቸው አንጻር የመንግሥት ልሳን ከመሆን አላለፉም።ነጻ ጋዜጣና ጋዜጠኝነት አለ ለማለት አያስደፍርም።ቢኖርም አብዛኛዎቹ በዚህም ሆነ በዚያ ከአንዱ የፖለቲካ ቡድን ወይም ከበርቴ ግለሰብና ኩባንያ፣ወይም የውጭ አገር መንግሥት ስርዓትና ጥቅም  ተሟጋች በመሆን የሚጮሁ ናቸው።

ጋዜጠኞች ብቻ ሳይሆኑ በተፈጥሮና በትምህርት ባገኙት  በኪነት ችሎታቸው ሕዝቡን የሚያነቁና የሚያስተምሩ ቢፈለጉ በጣም ጥቂቶች ናቸው።አብዛኛዎቹ በዋዛ ፈዛዛ፣ቀልድና አሉቧልታ፣ከማህበረሰቡ እድገትና ባሕል ጋር የማይጣጣም ትርከት ይዘው፣ በመድረክ ላይ እዬተውረገረጉ በዘፈን ፣በግጥም፣ በድራማና ፊልም በመሬት ላይ ያለውን ሃቅ  የሚሸፋፍኑ የስርዓቱ አደንዛዥ ኪኒን የሆኑ ብዙዎች ናቸው።ኪነት ሕዝብን ከድንቁርና ጨለማ

የሚያወጣ፣ሕዝቡን የሚያነቃና መብቱን አውቆ ለመብቱ እንዲታገል፣እውነትና ውሸቱን ለዛ ባለው መንገድ የሚጠቁም፣የአገር ፍቅር እንዲዳብር የሚያደርጉበት አንዱ መንገድ ነው። በአገራችን ግን ኪነት አደንዛዥ ኪኒን ከሆነ ቆይቷል።ሆኖም ግን ግዴታቸውን የተወጡ ቁጥራቸው አናሳ ቢሆንም መኖራቸው አይካድም።ለአብዛኞቹ ግን የሃብታምነት አቋራጭ መንገድ ሆኗል።የውጭ አገር ሃይሎች ወይም መንግሥታት የአንድን አገር ሕዝብ በተለይም ወጣቱን ትውልድ ከራሱ ባሕልና ታሪክ እንዲያፈነግጥና በስነልቦና ተማርኮ አገሩን እንዲጠላ ወይም ለባዕዳን ልቡን ብቻ ሳይሆን አገሩን አሳልፎ እንዲሰጥ ቀዳሚው ዘመቻ የሚከፈተው በኪነቱ ዙሪያ በሚያደርጉት ተልእኮ አስፈጻሚዎች በኩል ነው። ባሕልና ታሪኩን የማያከብር ትውልድ ደግሞ ለአገሩ ነጻነትና ልዑላዊነት አይጨነቅም። በኪነት ስም በሚተላለፈው ትዕይንት መካከል በሚተላለፈው የማስታወቂያ መልእክት የሚገኘው ገንዘብ ባለሙያተኞቹን ሚሊዬነርስ ብቻ ሳይሆን የሚዲያ ባለቤት እስከማድረግ አድርሷቸዋል።ቁም ነገርና የፈጠራ ሥራ ከሚከውነው ይልቅ በቀልድና አሉቧልት ላይ የተሰማራው አክብሮትና እውቅና ሲቸረው ይታያል።ወጣቱ ትውልድ በዋዛ ፈዛዛ እንዲጠመድ ከማድረግ ባለፈ ህይወቱን የሚቀርጽበት መልእክት የሚያገኝበት መንገድ አልሆነም፣ቢኖርም በጣም የጠበበ ነው።ብዙ የመከራ ጫና የተሸከመ ሕዝብ በሚኖርበት አገር የእነዚህ አሳሳቾች መኖር ሲጨመርበት ማህበረሰቡን ጭራሽ ያደነዝዘዋል።የኑሮ ውድነት ምንጭና ምክንያት የሆኑትም እነዚህ ቀልደኞች በቀላሉ በሚሰበስቡት ገንዘብ በሚገዙት ብልጭልጭ ሸቀጣ ሸቀጥ ገበያው በመዋጡ ነው። የከተማው ጽዳትና ውበት፣ለነዚህና ለውጭ አገር ቱሪስቶች ታስቦ እንጂ የሕዝቡን ችግር ለመፍታት አይደለም።የሕዝቡማ ጥያቄ መች የመዝናኛ ቦታ ሆቴልና ፓርክ ሆነና?እዬዬም ሲደላ ነው!

የዕድገትና የልማት መለኪያው የነሱ አስረሽ ምችው ኑሮ ሆኗል።ለአገር ጠቃሚ የሆነ ከፍተኛ ትምህርት ተምሮ ድንጋይ ፈላጭ በሆነበት አገር እነዚህ የቀልድና የፌዝ ፈላስፎች የሚከበሩበት አገር ሆኗል። የሚገርመው ከባለጸጎቹ አገራት በተለይም ከአሜሪካኖቹ የመድረክ (የፊልም ኢንዱስትሪ) ተዋንያን ጋር እራሳቸውን አስቀምጠው ሴሌብሪቲስ፣ እያሉ መኮፈሳቸው ነው።እንዲህ ነው የባሕልና የስነልቦና ምርኮኛነት ማለት።በአገራችን እውነተኛዎቹ ኪነታውያን የሕዝብ ልሳኖች ተገቢው ስማቸው ጠቢባንና አጫዋቾች የሚለው ነው።አጫዋች ማለት ደግሞ ፣ደጉንና ክፉውን እያሳዩ የሚያጽናና ብሎም መካሪና አስተማሪ ማለት ነው።የጥንት ዘፋኞች፣ ቅኔ ዘራፊዎችና፣ተውኔታውያን ለማህበረሰቡ ንቃተህሊና ብዙ አበርክተዋል። አሁንም ቢሆን የነዛን ፈለግ የተከተሉ አሉ።

የሕዝብ ወገን የሆኑ፣የኪነት ባለሙያዎች፣ዘፋኞች፣ፀሓፊዎች በችግር አሮንቋ ተዘፍቀው በመጨረሻውም ታመው ህክምና አጥተው የሚሞቱበት አገር ነው። ለሙያው ያደሩ ጋዜጠኞችም ኑሯቸው የወከባ ኑሮ ሆኗል፤ የቻሉት ይሰደዳሉ፣አለያም በእስር ቤት ይማቅቃሉ።በአንጻሩ ደግሞ የጋዜጠኝነት ጭንብል ያጠለቁት እበላባዮች ጥቅም ባለበት ቦታ ሁሉ እንደ ውሻ አነፍንፈው ብቅ ይላሉ።ጊዜ ከሰጠው ጋር ለማናፈስ የሚቀድማቸው

የለም። ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ሰበር ዜና እያሉ ካቀረቡት ዕርእስ ጋር የማይሄድ አቶፈንቶ በማቅረብ በየዋሆች ጀርባ ገንዘብ ይሰበስባሉ።የመንግሥትንም ፕሮፓጋንዳ ይነዛሉ። ከዚያም ከዚህም ገንዘብና ጥቅም ካገኙ ይሉኝታ የላቸውም፤እዚያም ዘው፣ እዚህም ዘው ነው።ለ27 ዓመታት በዘመነ ወያኔ ጊዜ እጅና ጓንት ሆነው ሲጮሁ የነበሩትና ከአራት ዓመት ወዲህ ከዘመነ ኦሕዴድ መራሹ ተረኛ ቡድን ጋር እጅና ጓንት ከሆኑት ጋር ጥምረት ፈጥረው የአብይ አህመድን ጎሰኛ መንግሥት የከለላ ሽፋን ሲሰጡት ቆይተዋል፣ በመጮህ ሕዝቡን ሲያወናብዱ ኖረዋል። አብይ አህመድ እነዚህኑ በአገር ውስጥና በውጭ አገር የሚኖሩ ጋዜጠኞችና የኪነት ሰዎች ተብዬዎቹን ባለውለታዎች በቤተመንግሥቱ ሰብስቦ ላደረጉለት ሕዝቡን የማወናበድ አስተዋጽኦ እውቅናና ሽልማት ሰጥቷቸዋል።ግማሾቹንም በያሉበት አገር ተቃዋሚ መስለው የስለላ ሥራ እንዲሠሩ እንደመደባቸው የሚገልጸው ምስጢር እነሱ ከኢትዮጵያ ሳይወጡ ሾልኮ ወጥቷል።እነሱም ሥራቸውን ጀምረዋል፤ በተቃዋሚው ድንኳን ውስጥ ሰርገው በመግባት የተቃውሞ ድምጽ እያሰሙ ነው።ሲከፋሽ ወደኔ ሲደላሽ ወደሱ ነውና ሰሞኑን የአብይ መንግሥት የተደበቀ መልኩ ሲጋለጥና አብረውት የተሰለፉት አንዳንዶቹ ጭምር ግራ ተጋብተው ዓይንህን ላፈር ሲሉት፣ሙቀቱን እየለኩ እነይሉኝታ ቢሱ ጋዜጠኞችና የመድረክ ሰዎች ከመቅጽበት እጥፍ ብለው የተቃዋሚውን ጩኸት እየጮሁ ብቅ ብለዋል።

በሌላው በኩል ምንም እንኳን የጋዜጠኝነት ሙያ ባይኖራቸውም የወገናቸውን ብሶትና መከራ፣የመንግሥትን ገበናና እውነተኛ ገጽታ ፣አገራቸው የገባችበትን አደጋ በመተንተን እንዲታወቅ ገንዘባቸውን፣ጊዜያቸውን፣እውቀታቸውን በማፍሰስ በጽሑፍና በራዲዮ እንዲሁም በዩቲዩብ የሚያስተላልፉ የሕዝብ ጠበቆች የሆኑ አገር ወዳዶች ለሚደርስባቸው ስድብና ዛቻ ሳይንበረከኩ ለብዙ ዓመታት የቆሙለት እውነት ድል እዬመታ መጥቷል።ከመሸነፍ ይልቅ በያገሩ ተበራክተዋል።የእነዚህን ጥረትና ድካም ለማኮላሸት በአድርባዮች የማይሸረብ ተንኮልና ስም ማጥፋት የለም። አሁንም አድርባዮቹ ተልእኮ ተሰጥቷቸው የተሰማሩትም በነዚህ ላይ ነው።ሜዳውን ለመቀማት የማይፈነቅሉት ድንጋይ የለም።አካፋን አካፋ በማለት የአድር ባይነትን ባሕል ለማሶገድ አድርባዮችን ፊት መንሳት የትግሉና የለውጡ አካል ሊሆን ይገባል።ወደፊት እንዳስፈላጊነቱ ካስፈለገ ስማቸውን በዝርዝር የምናቀርበው ይሆናል።

ታዲያ ያገራችንን ጋዜጠኞችና የኪነት ሰዎች ምን ብለን እንጥራቸው?አፈንጉስ፣አፈ መንግሥት፣አወዳሽ፣አደንዛዥ፣እበላባይ፣አውደልዳይ፣አዝማሪ፣አጫፋሪ፣ ፋና ወጊ፣እውነት ተናጋሪ፣ አስተማሪ፣ቃል አቀባይ ወይስ ሰላይ? መልሱ እንደዋሉበት ሜዳ ሕዝብ የሚሰጣቸው ስያሜ ይሆናል።

እውነት ተናጋሪዎችን፣ፋና ወጊና አስተማሪ ደፋር ሕዝባዊ ጋዜጠኞችን፣ደራስያንን የኪነትና የመድረክ ሰዎችን ያብዛልን!!

በስውድን የኢትዮጵያ አንድነት ራዲዮ የስነጽሑፍ ክፍል የተዘጋጀ